# የዐቢይ የድጋፍ ሰልፍና አደገኛ ድብቅ ፀረ ሕዝብ ሴራው!

ሽፍጠኛው፣ ሴረኛው፣ ቁማርተኛው፣ አጭበርባሪው፣ አወናባጁ ወያኔ ከዐቢይ ጋር ቅራኔ ያለው አስመስሎ በመናኘትና በጎን ደግሞ ሕዝቡ ለዐቢይ አዝኖ ራርቶ ዐቢይን እንዲደግፍ እየገፋፋ በዐቢይ በኩል ማርኮ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከእግሩ ስር ለመጣል በማሰብ ሕዝቡ ለዐቢይ አሥተዳደር የጋለ ድጋፉን በነቂስ ወጥቶ በአደባባይ ሰልፍ የፊታችን ቅዳሜ 16,10,2010 ዓ.ም. ቀን እንዲገልጽ እና ዐቢይን እየተቃወሙ ያሉ የሚባሉትን "ለውጥ አደናቃፊ!" በሚል የተውኔት ስማቸው የሚጠሩትን ደግሞ እንዲያወግዝ በማድረግ ይሄንንም ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማሳየት አገዛዙ ከሕዝብ ጋር ያለውን ችግር የፈታ፣ ሰላም ያወረደ፣ ስምምነት የፈጠረ፣ እርቅ ያመጣ፣ መግባባት ላይ የደረሰ አስመስሎ በማሳየት ወይም የጋለ የሕዝብ ድጋፍ ያለው አዲስ መንግሥት ሥልጣን ላይ ያለ አስመስሎ በማቅረብ ለአሜሪካ መንግሥት የቀረቡ የ HR 128 እና SR 168 የውሳኔ ሐሳቦችን ለማጨናገፍ፣ አገዛዙ ከሕዝብ ጋር በፈጠረው ችግር ምክንያት እርዳታና ብድር የከለከሉትን ምዕራባውያን መንግሥታትን እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን ለማግባባት ለማሳመን እጅግ እጅግ አስደናቂ በሆነ አፈጻጸም በከፍተኛ ቅንጅት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በእነኝህ ሰልፎች ተገኝቶ ለሐሰተኛው ለአስመሳዩ የዐቢይ አሥተዳደር ድጋፍ መስጠት ማለት ስንት ድካም፣ ስንት መሥዋዕትነት የተከፈለበት ሕዝባዊ ትግልህን ተጨናግፎ እንዲቀር መስማማት፣ ወያኔ የጭቆና አገዛዙን የሚመልስበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ዕድል እንዲያገኝ መርዳት፣ በጥቅሉ እራስን ማጥፋት መሆኑን ተረድተህ በወንበዴዎች በነፍሰ በላዎች ለተሞላው ለአስመሳዩ፣ ለቅጥረኛው፣ ለተዋኙ፣ ለአወናባጁ፣ ለአታላዩ፣ ለቅቤ ምላሱ፣ ለደላላው ለዐቢይ አሥተዳደር የድጋፍ ሰልፍ ከመውጣት ትታቀብ ዘንድ አጥብቄ አሳስባለሁ እማጸናለሁም!!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ይሄ አጋጣሚ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተደረገ ባለው ከፍተኛ የማስመሰል ጨዋታ በተለያየ ምክንያት ተደልለውና ተታለው በአንተ ላይ ክህደት በመፈጸም በድብቅ አሰላለፋቸውን ዐቢይን በጭንብልነት ከሚጠቀመው የወያኔ አገዛዝ ጎን ያደረጉት ታዋቂ ሰዎች ነን፣ አርቲስቶች (ከያኒያን) ነን ፣ ፖለቲከኞች (እምነተ አሥተዳደራውያን) ነን ፣ አክቲቪስቶች (ስሉጣን) ነን፣ ጸሐፍያን ነን፣ ተንታኞች ነን፣ የፖለቲካ ቡድን ነን ባይ ገልቱዎች እነማን እንደሆኑ ለመለየት ዕድል ሰጥቶሀልና በታዋቂነታቸው በተሰሚነታቸው አንተ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ሰልፉ ላይ ተገኝተህ ድጋፍህን እንድትገልጽ እየቀሰቀሱህ፣ እየገፋፉህ፣ እየወሰወሱህ ያሉት ቅጥረኞች እነማን እንደሆኑ ለይተህ እወቃቸው!!!

ሌላው ደግሞ ፖለቲካን (እምነተ አሥተዳደርን) ሳታውቁ ፖለቲከኛ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ነኝ ፣ ጥልቅ ዕይታ (insight) ሳይኖራቹህ ጸሐፊ ነኝ ተንታኝ ነኝ ስሉጥ ነኝ ዘጋቢ (ጋዜጠኛ) ነኝ የምትሉና ወያኔ እንደ አሻንጉሊት እንደፈለገ እየተጫወተባቹህና እየተጠቀመባቹህ ያላቹህ ግለሰቦችና ቡድኖች ምኑንም ባልተረዳቹህት ጉዳይ ላይ ሕዝብ ለዐቢይ አሥተዳደር ድጋፍ እንዲሰጥ በመገፋፋት እያደረጋቹህት ካላቹህት ጥረት ትታቀቡ ዘንድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም አጥብቄ እለምናለሁ፡፡

አውቃለሁ ብዙዎቻቹህ ለዚህ ተልእኮ የተሰለፋቹህት ተገዝታቹህ ወይም በተለያየ ጥቅም ተደልላቹህ እንደሆነ፡፡ ግን እንዲያው እባካቹህ ለስማቹህ፣ ለግለ ታሪካቹህ፣ ለሕሊናቹህ ጥቂት እንኳ አስቡና እየተባበራቹህት ያላቹህት አዲስ ከሌላ ዓለም የመጣ ሳይሆን ራሱ ትናንት የነበረውና አንድም ቀን ለቃሉ ታምኖ ባለማወቁ የምታውቀው ወንበዴ የጥፋት ኃይል እንደሆነ ተረድታቹህ ከመጃጃልና ሕዝብን ለማጃጃል ከመጣር ታቀቡ??? እባካቹህ እባካቹህ እባካቹህ???

ወደ ለውጥ መሒጃው መንገድ ፈጽሞ ይሄ አይደለም፡፡ ይሄ ማጭበርበር ማወናበድ ነው፡፡ እንዴት ሊከሰትላቹህ እንዳልቻለ አላውቅም እንጅ የሁነቶችን ቅደም ተከተል፣ የዐቢይንና የወያኔን መናበቦችን፣ የሁነቶች መከወኛ ሰዓቶችን (timing) ልብ ብላቹህ ብታጤኗቸው እያንዳንዷ ነገር ወያኔና ዐቢይ ቁጭ ብለው መክረው፣ አብረው ዶልተው፣ አቀናብረው፣ አቀናጅተው ነው እየሠሩ ያሉት፡፡ አንደኛው ክፉ ገጸባሕርይውን እየተወነ ሌላኛው በጎ ገጸባሕርይውን እየተወነ ነው ሕዝብን እያጃጃሉ ያሉት፡፡ ሌላ ምንም ነገር የለም!!!

እናም በምታዩትና በምትሰሙት አትታለሉ??? አንድም ለለውጥ እየተደረገ ያለ የለውጥ ሒደት የለም!!! የተውኔት (የቴአትር) ወሬ ብቻ ነው ያለው፡፡ ወሬውን ትታቹህ መሬት ላይ ያለውን ሃቅ ብቻ ተመልከቱ፡፡ ለገዛ ቅዠታችን ተገዥ ሆነን ወይም ራሳችንን የቀን ቅዠት ውስጥ ከተን ከዚህ ከጣፋጩ የቀን ቅዠታችን መንቃት ስላልፈለግን ነው እንጅ የነዐቢይ እንቅስቃሴ ሐሰተኛ ወይም የማስመሰል ማወናበድ መሆኑን ለመለየት ይሄንን ያህል የሚያስቸግር ነገር አልነበረም፡፡

ወያኔ/ዐቢይ ለለውጥ የቆረጡ ቢሆኑ ኖሮ የለውጥ እርምጃዎችን ማለትም አፋኝ አሳሪ ገዳቢ አዋጆቻቸውን በመሻር፣ ሁሉም የተቃውሞ ኃይል የተሳተፈበት የፖለቲካዊ መፍትሔ ማመንጫ መድረክ በማመቻቸት፣ ብሔራዊ እርቅ በመጥራት፣ የሽግግር መንግሥት በመመሥረት ወዘተረፈ. የለውጥ እርምጃዎችን በተግባር አድርገው በማሳየት ለለውጥ የቆረጡ መሆናቸውን በተግባር ያረጋግጡ ነበር እንጅ እጅግ ስልታዊ በሆነ አኪያሔድ አንዱ ክፉ ገጸባሕርይ ሌላው በጎ ገጸባሕርይ እየተወኑ ተጠያቂነትንና ቅጣትን በማያስከትል ሁኔታ ራሳቸውን በመኮነንና በማውገዝ፣ ለሕዝቡ ስሜቱን የሚነካ ንግግር በማድረግ፣ ሕዝቡ ሊሰማው የሚፈልገውን ነገር በመንገር፣ ብሶቱን አሰማምሮ በመናገር ሕዝብን በባዶ ወሬ ሲደልሉ ሰንብተው ሲያበቁ ሕዝቡ በነቂስ ሰልፍ ወጥቶ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ለማድረግ ይሄንን ጥረት አያደርጉም ነበረ፡፡

እስረኛ እንደመፍታት ያሉ የማታለያ ተግባራትን በመፈጸም ሕዝብን በባዶ ወሬ አጥግበው ከላይ የጠቀስኳቸውን ተጨባጭ የለውጥ እርምጃዎችን ሳይወስዱ ሕዝቡ ድጋፉን እንዲሰጣቸው በከፍተኛ ደረጃ እየተሚሟቱ ያሉት ለተጨባጭ ለውጥ የቆረጡ ባለመሆናቸውና አታላዩን፣ አወናባጁን፣ አስመሳዩን፣ ሐሰተኛውን መንገድ በመምረጣቸው ነው፡፡ በመሆኑም እያደረጋቹህለት ያለው ትብብርና ድጋፍ ለሀገርና ለሕዝብ አስከፊ ኪሳራን እንጅ ትርፍ የሚያመጣ አይደለም!!! እባካቹህን ንቁ!!!!....

እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቃቹህ፦ ወያኔ/ኢሕአዴግ ለለውጥ የቆረጠ መሆኑን መግለጫ አውጥቶ ካወጀና ምሎ ከተገዘተ በኋላ ከላይ የጠቀስኳቸውን ተጨባጭ የለውጥ እርምጃዎችን እንዳይወስድ ማን ከለከለው??? ማን እጁን ያዘው???

አያቹህ እንዲህ ተብሎ እንዳይጠየቅና የተግባር እንቅስቃሴ ሳያደርግ ሕዝብን በወሬ ብቻ ደልለው ያጋጠማቸውን ችግር መሻገር ማለፍ ስላሰቡ ስለፈለጉ ነው አንደኛው ለውጥ የማይፈልግ የለውጥ አደናቃፊ ክፉ ገጸ ባሕርይን ይዞ ሌላኛው ደግሞ የለውጥ ሐዋርያ በጎ ገጸባሕርይን ይዞ በመተወን "እከሌ ለምንድን ነው ይሄን ይሄን የለውጥ እርምጃዎችን የማይወስደው?" ብለን ጠይቀን እኛው ራሳችን "እነ እከሌ እያሉ እነሱ እያደናቀፉት በየት በኩል ሊያደርግ ይችላል?" ብለን ለራሳችን መልስ እየሰጠን በዝምታ በመመልከት ዕድሜያችንን እንድንፈጅ እነሱም የሥልጣን ዘመናቸውን ማራዘም የሚችሉበትን ስልት ነው ነድፈው እየተንቀሳቀሱ ያሉት፡፡

ወያኔ/ኢሕአዴግ ለሕዝብ ቅንጣት ታክል ክብር የሌላቸው የባለጌዎች፣ የውርጋጦች፣ የወንበዴዎች ስብስብ በመሆኑና በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያን ሕዝብ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚንቁት ነው እንዲህ በነፍስ በሥጋው እየተጫወቱበትና እየቀለዱበት ያሉት፡፡

በአሁኑ ሰዓት ወያኔ ከላይ በገለጽኩላቹህ ትወና ሕዝብን አወናብዶ እስትንፋሱን ለማቆየት ያለ የሌለ አቅሙን ነው አሟጦ እየተጠቀመ ያለው፡፡ ሹም ሽረቱና ሌላው ሌላው ነገር ሁሉ ሕዝብን አታሎ በማሳመን ከጎናቸው እንዲሰለፍ ለማድረግ

የሚደረግ የውሸትና ለጥቂት ጊዜ የሚቆይ የማወናበጃ ተግባር ነው፡፡ ከቆይታ በኋላ ሁሉም ነገር ወደነበረበት ይመለሳል፡፡ የአባዱላንና የበረከት ስምኦንን ከሳምንት በላይ ያልዘለቀ የውሸት ስንብትን ያስታውሷል፡፡

እናም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! የአወናባጆን የዐቢይን ነገር እርግፍ አርገህ ጥለህ ፈጥነህ ወደ ትግልህ ተመለስና ትግልህን አጠናክረህ ቀጥል!!! ከወያኔ መፍትሔ አገኛለሁ፣ ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ለውጥ አገኛለሁ ብለህ ፈጽሞ ተስፋ አታድርግ!!! ፈጽሞ ሊሆን የማይችል የቀን ቅዠት ነውና!!!

መድኃኔዓለም ክርስቶስ የእነኝህን ኢጋንንት ሴራ፣ ሸፍጥ፣ ደባ ዘርዝሮ፣ አክሽፎ፣ ሽሮ፣ ደምስሶ ከቀንበራቸው ይገላግለን! አሜን!!!

በዚህ አጋጣሚ ተመሳሳይ የሆነ ለሐሰተኛውና ለደላላው የዐቢይ አሥተዳደር የድጋፍ ሰልፍ በሰሜን አሜሪካም ሆነ በሌላ ቦታ ለማድረግ የተዘጋጃቹህ የዋሃን ወገኖች እባካቹህ ከቀን ቅዠታቹህ ንቁ!!! ኋላ ለከባድ ጸጸት የሚዳርጋቹህን ስሕተት ከመፈጸም ታቀቡ!!!

ወያኔ ከሁለት ሦስት ወራት ወዲህ የትኛውም ድረገጽ የኔን ጽሑፍ እንዳይለጥፍ በሚደልልበት ደልሎ ስለያዛቸውና ድረገጾች ጽሑፎቸን መለጠፍ ስላቆሙ ይሄንን አንገብጋቢ መልዕክትና ማሳሰቢያ በየፌስ ቡክ አካውንታቹህ (በየመጽሐፈ ገጽ መዝገባቹህ) ሼር በማድረግ (በመጋራት) ለሕዝባችን ታደርሱ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com